የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲
አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No 10
ADDIS ABABA, 9th March, 2022

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፬፻፺፩/፪ሺ፲፬

የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና መጠንን ለመወሰንና ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................................ገጽ ፲፫ሺ፱፻፴፰

**Content**

Regulations No 491/2022

Vehicles Weight and Dimension Determination and Regulation Council of Ministers Regulation.........................................Page 13938

## ደንብ ቁጥር ፬፻፺፩/፪ሺ፲፬

## የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና መጠንን ለመወሰንና ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ አንቀፅ ፳፰ መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደት እና መጠንን ለመወሰን እና ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፺፩/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

## REGULATION NO. 491/2022

## VEHICLES WEIGHT AND DIMENSION DETERMINATION AND REGULATION COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 28 of the Transport Proclamation No. 468/2005.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Vehicle Weight and Dimension Determination and Regulation Council of Ministers Regulation No. 491/2022."

### 2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 77.00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Scanned by CamScanner

፩/ “**አዋጅ**” ማለት የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር ፬፻፷፰/፲፱፻፺፯ ነው፤

፪/ “**የተጣመረ ተሽከርካሪ**” ማለት የባለሞተር ተሽከርካሪንና ከተሽከርካሪ ጋር የተያያዘውን ተሳቢ አጣምሮ የያዘ ተሽከርካሪ ነው፤

፫/ “**ያልተለመደ ጭነት ወይም ተሽከርካሪ**” ማለት በዚህ ደንብ ውስጥ ከሚፈቅደው ከፍተኛ መጠን ወይም ልኬት በላይ የማይነጣጠሉ ጭነቶችን የሚሸከሙ ተሽከርካሪዎች ወይም ተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች ማለት ነው፤

፬/ "**ያልተጣመረ ነጠላ ተሽከርካሪ**" ማለት ተሳቢ የሌለው በረዥም ቻሲስ የተዋቀረ አንድ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

፭/ “**አክስል**“ ማለት በተሽከርካሪው ስፋት ላይ ቀጣይነት ያለው ወይም የሌለው የተዘረጋ ዘንግ ሆኖ የተሽከርካሪዎቹ መንኮራኩሮች የሚሽከረከሩበት እና ተሽከርካሪው ወደፊት በሚጓዝበት ጊዜ የሽከርከሪቶች ቀጥተኛ ማዕከላዊ መስመሮች በአንድ ወጥ የቀኝ ማዕዘን አቀባዊ ማዕከላዊ መስመር የሚይዝ ማለት ነው፤

፮/ “**የአክስል ክብደት**” ማለት በማንኛውም አክስል ላይ ያሉ የሁሉም ጎማዎች አጠቃላይ ክብደት ድምር ነው፤

፯/ “**አክስል ክፍል**” ማለት ከተሽከርካሪ ጋር በተያያዘ የሁለት ወይም ከዚያ በላይ ትይዩ አክስሎች ስብስብ ሆኖ ለተሽከርካሪው እንደ አንድ የአክስል ክፍል ሆነው እንዲያገለግሉ የተሳሰሩ ናቸው፤ በተሳቢ ላይ የተገጠሙ ከሆነ ደግሞ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ

1/ **“Proclamation”** means Transport Proclamation No. 468/2005;

2/ **“Articulated Vehicle”** means a combination of vehicles comprising of a motor vehicle and a semi-trailer;

3/ **“Abnormal Load or Vehicle”** means a vehicle or combination of vehicles carrying an indivisible load that exceeds the permissible maximum mass or the dimensions prescribed in this Regulation;

4/ **Single Vehicle (Rigid Chases)**:- Means a motor vehicle with rigid single chases having no trailer;

5/ **“Axle”** in relation to a vehicle means a bar or beam or a set thereof, whether continuous across the width of the vehicle or not, about which the wheels of the vehicle rotate, and which is so placed that, when the vehicle is travelling straight ahead, the vertical centre-lines of such wheels are in one vertical plane at right angles to the longitudinal centre-line;

6/ **“Axle Mass”** means the sum of the wheel mass of all wheels on any axle;

7/ **“Axle Unit”** in relation to a vehicle, means a set of two or more parallel axles of such vehicle which are so interconnected as to form a unit; and in the case of a trailer, two or more

Scanned by CamScanner

፲፩/ **"ክብደት"** ማለት ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የተሽከርካሪው የተጣመሩ ጎማዎች በክብደት መመዘኛ መሳሪያ በኪሎ ግራም የሚለካውን ክብደት ጨምሮ በተሽከርካሪው ወደ መንገድ የሚተላለፈውን ኃይል ለመወሰን የሚያገለግል ነው፤

፲፪/ **"የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት"** ማለት በዚህ ደንብ የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት ነው፤

፲፫/ **"ከክብደት በላይ"** ማለት የአንድ ተሽከርካሪ የአክስል ክብደት ወይም የአክስል ክፍል ክብደት ወይም የተሽከርካሪው ወይም የተጣመረው ተሽከርካሪ ጠቅላላ ክብደት በዚህ ደንብ ከተቀመጠው የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት በላይ ሲሆን ነው፤

፲፬/ **"ግማሽ ተሳቢ"** ማለት ለጭነት ማመላለሻ የሚያገለግልና በሌላ ባለሞተር ተሽከርካሪ የሚሳብ የፊት አክስል የሌለው ሆኖ ቢያንስ ፲፭ በመቶ የሚሆነው የተሽከርካሪውም የጭነቱም ክብደት በጎታች ተሽከርካሪ ላይ እንዲያርፍ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ እንዲሳብ ተደርጎ የተሰራ ተሽከርካሪ ነው፤

፲፭/ **"ነጠላ አክስል"** ማለት በአንድ ዘንግ የተያያዙ ቢያንስ ሁለት ጎማዎችን የያዘ አንድ አክስል ነው፤

፲፮/ **"ጥንድ አክስል"** ማለት በመንገድ ላይ የሚያርፈው ክብደት በተመጣጠነ መልክ እንዲሰራጭ ታስቦ የተነደፈ ከ፩ነጥብ፪ ሜትር እስከ ፪ነጥብ፭ ሜትር በሆነ ርቀት ውስጥ የተሳሰሩ ሁለት አክስሎች ስብስብ ነው፤

11/ **"Mass"** in relation to ths Regulation means the combination of the tyres of a vehicle together with the load that it is carrying measured in kilogram by the weighing device and is used to determine the force exerted by that vehicle on the pavement;

12/ **"Maximum Permissible Mass"** in relation to a vehicle means the maximum mass allowed in accordance with this Regulation;

13/ **"Overload"** means when the axle mass, axle unit mass or the gross weight of the vehicle or combination of vehicles exceeds the maximum permissible mass as set forth in this Regulation;

14/ **"Semi-Trailer"** means a trailer having no front axle and so designed that at its front part is attached to the rear of a vehicle and least 15 percent of its tare is super-imposed on and borne by the vehicle drawing it;

15/ **"Single Axle"** means one axle with at least two pneumatic tyres;

16/ **"Tandem Axle Unit"** means two axles suspended together with a spacing between them ranging from 1.2 metre to 2.5 metre; and interconnected in such a manner that any load imposed upon them will

Scanned by CamScanner

፲፯/ **“ባለሶስት አክስል”** ማለት በመንገድ ላይ የሚያርፈው ክብደት በተመጣጠነ መልክ እንዲሰራጭ ታስቦ የተነደፈ ከ፩ነጥብ፪ ሜትር እስከ ፪ነጥብ፭ ሜትር በሆነ ርቀት ውስጥ የተሳሰሩ ሶስት አክስሎች ስብስብ ነው፤

፲፰/ **“የመሪ አክስል”** ማለት ተሽከርካሪው የሚጓዝበትን አቅጣጫ ለመቆጣጠር ሲባል አሽከርካሪው የሚቆጣጠረው መሪ ያረፈበት አክስል ነው፤

፲፱/ **“መመዘኛ መሳሪያ”** ማለት ሚዛን ወይም ማንኛውም ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጥ ሌላ መሳሪያ ሆኖ በቋሚ ቦታ የተገጠመ ወይም ተንቀሳቃሽ የሆነ የተሽከርካሪዎችን ክብደት ከጭነታቸው ጋር ወይም ሳይጭኑ ለመመዘን የሚያገለግል እና ቋሚ፣ የእንቅስቃሴ ላይ ወይም ተንቀሳቃሽ ሚዛን ተብሎ የሚለይ መሳሪያ ሲሆን ለግል መገልገያነት ብቻ አገልግሎት የሚሰጡ ሚዛኖችን አያካትትም፤

፳/ **“ሚዛን ጣቢያ”** ማለት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ ደንብ የሚሸፈን ተሽከርካሪን ለመመዘን የከለለውና መመዘኛ መሳሪያ የተተከለበት ስፍራ ነው፤

፳፩/ **“የተሽከርካሪ ባለቤት”** ማለት በዚህ ደንብ የሚሸፈነውን ማንኛውንም ተሽከርካሪ በባለቤትነት፣ በኪራይ፣ በሽያጭ ውል፣ በንግድ ወይም በትራንስፖርት ማህበራት አማካኝነት ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ይዞ የሚገለገልበት ማንኛውም ሰው ነው፤

automatically be distributed between the axles of the unit;

17/ **“Tridem Axle Unit”** means three axles suspended together with a spacing between them ranging from 1.2 metre to 2.5 metre; and interconnected in such a manner that any load imposed upon them will automatically be distributed between the axles of the unit;

18/ **“Steering Axle”** means an axle the steering of which is controlled by the driver of a vehicle;

19/ **“Weighing Device”** means a weighbridge or any other device, whether installed in a fixed position or mobile, which is intended for use for determining the mass of vehicles, laden or unladen; and may be classified as static, weigh-in-motion or mobile Weighing Device in exclusion of weighing devices used for private purpose only;

20/ **“Weigh Station”** means the entire premises where the Competent Authority has installed a weighing device and designated so for weighing vehicles covered under this Regulation;

21/ **“Vehicle Owner”** means, for the purpose of this Regulation, any person operating a vehicle covered under this Regulation either by owning, rent, purchase, hire, being enrolled in a transport association,

Scanned by CamScanner

or using the vehicle through any other arrangement;

፳፪/ **"ልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪ"** ማለት ከተሽከርካሪው ስሪትም ሆነ አገልግሎት እየሰጠ ከሚገኝበት ዓላማ አንጻር የጦር መሳሪያዎች በቋሚነትም ሆነ በጊዜያዊነት የተገጠሙበት፣ ከቀለሙና ከቅርጹ አንጻር ለወታደራዊ አገልግሎቶች ብቻ የሚውል ተሽከርካሪ ሲሆን ንብረትነታቸው የወታደራዊ ተቋምም ቢሆን መደበኛ የሆኑ በዚህ ደንብ የተገለጹትን የጭነት ተሽከርካሪዎችን አይጨምርም፤

22/ **"Special Military Vehicle"** means a vehicle manufactured for sole purposes of military activities as equipped with armaments fixed to it permanently or temporarily; and does not include those ordinary vehicles of the military organ which are similar to those covered under this Regulation;

፳፫/ **"ባቡር አውቶብስ"** ማለት የከተማ ውስጥ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ ለመስጠት ታስቦ የተሰራ፣ በአንድ በተወሰነ የጉዞ መስመር ብቻ የሚጓዝና እንደባቡር ፉርጎ ረዥም አካል ኖሮት በርካታ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ የሚችል አውቶብስ ነው፤

23/ **"Bus-Train"** means a vehicle designed for the purpose of urban mass transport services; operated in a dedicated line and having train featured long body with an ultra-capacity to carry many passengers at a time;

፳፬/ **"የተተወ (የተጣለ) ቁስ"** ማለት በብልሽት ወይም በሌላ ማንኛውም ምክንያት ፈጽሞ ተመልሶ አገልግሎት ሊሰጥ የማይችልና የተጣለ ወይም የተተወ ተሽከርካሪ ሲሆን ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ማንኛውንም የተጣለ ብረታብረትና ሌሎች ደረቅ ቆሻሻ ይጨምራል፤

24/ **"Refuse"** means an abandoned vehicle due to damage or any other reason and that cannot be put back to service and shall, for the purpose of this Regulation, include any abandoned metal items or garbage;

፳፭/ **"የተበላሸ ተሽከርካሪ"** ማለት በሞተሩ ወይም በአካሉ ወይም በሁለቱም ወይም በሌላ ማንኛውም ክፍሉ ላይ ጉዳት ደርሶበት በራሱ ኃይል ሊነዳ የማይችል ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፤

25/ **"Damaged Vehicle"** means a vehicle that cannot be driven due to damages to its motor or body parts or both;

፳፮/ **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

26/ **"Ministry or Minister"** means the Ministry or Minister of Transport and Logistics;

Scanned by CamScanner

፳፯/ "በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል" ማለት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ነው፤

፳፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት የተሰጠው ተቋም ነው፤

፳፱/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የተሰጡት ትርጓሜዎች በዚህ ደንብ ላይ ተፈጻሚ ናቸው፤

፴/ በዚህ ደንብ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

፩/ ይህ ደንብ በማናቸውም የኢትዮጵያን መንገድ በሚጠቀሙ ጠቅላላ ክብደታቸው ከ፫ሺ፭፻ ኪሎ ግራም በላይ በሆነ ተሽከርካሪዎች፣ የተጣመሩ ተሽከርካሪዎች እና ተሣቢዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በእሳት አደጋ መከላከያ ተሽከርካሪዎች፣ የተፈጥሮ አደጋ መከላከል ሥራ ላይ በተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፣ በድንገተኛ አደጋ የወደሙ መሰረተ-ልማቶችን በመገንባት ሥራ ላይ በተሰማሩ ተሽከርካሪዎች፣ ኢትዮጵያ በተፈራረመቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መነሻነት የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች፣ የግንባታ ሥራ በሚከናወንበት አካባቢ የሚንቀሳቀሱ የግንባታ ተሽከርካሪዎች እና በልዩ ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ላይ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

፬. <u>ስለ መመዘኛ መሳሪያዎች</u>

፩/ በዚህ ደንብ የሚሸፈን ማንኛውም መመዘኛ መሳሪያ ብቃት ባለው ሰው በሦስትዮሽ ትራንስፖርት እና ትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም ደረጃ መሰረት ፈቃድ ማግኘት

27/ **"Competent Authority"** means the Ethiopian Roads Administration;

28/ **"Person"** shall mean any natural or juridical person;

29/ The definitions provided under Article 2 of the Proclamation shall apply to this Regulation;

30/ Any expression in the masculine gender includes the feminine gender.

3. <u>**Scope of Application**</u>

1/ This Regulation shall apply to all motor vehicles, articulated vehicles and trailers with gross vehicle or combination mass exceeding 3500 kilogram using any road in Ethiopia.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the provisions of this Regulation shall not apply to motor vehicles designed and used for fire-fighting; natural disaster relief operations; emergency infrastructure restoration purposes; vehicles operating based on international agreements to which Ethiopia is a party; vehicles engaged in construction activities on construction sites, and Special Military Vehicles.

4. <u>**Weighing Devices**</u>

1/ Any weighing device installed or used in accordance with these Regulations, shall be certified by a competent person as to comply with the relevant Tripartite Transport and Transit

Scanned by CamScanner

አለበት፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም መመዘኛ መሳሪያ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በሶስትዮሽ ትራንስፖርት እና ትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም የመመዘኛ መሳሪያዎች አጠቃቀም ደረጃ መሠረት ተመርምሮ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት አለበት፣

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የሦስትዮሽ ትራንስፖርት እና ትራንዚት ፋሲሊቴሽን ፕሮግራም የመመዘኛ መሣሪያዎች አጠቃቀም ደረጃ ተግባራዊ እስከሚደረግ ድረስ የመመዘኛ መሣሪያዎች ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን የተሰጠው አካል በሚያወጣው ደረጃ መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፤

፬/ የሚዛን ጣቢያ አስተዳዳሪ የመመዘኛ መሳሪያው በተገቢው መንገድ እንደሚሰራ የሚያረጋግጠውን ሰርቲፊኬት ማሳየት አለበት፡፡

## ፭. <u>የተሽከርካሪን ክብደት እና መጠን ስለመወሰን</u>

፩/ ማንኛውም የተሽከርካሪ አስመጪ ወይም አምራች በዚህ ደንብ የተሸፈነን ማንኛውንም ተሽከርካሪ አገልግሎት ላይ ከማዋሉ ወይም እንዲውል ከማድረጉ በፊት የተሽከርካሪውን ክብደት እና መጠን በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት ሥልጣን ባለው አካል ዘንድ ማስመዝገብ አለበት፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት አንድ ተሽከርካሪ ለምዝገባ ሲቀርብ ሚኒስቴሩ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ተሽከርካሪውን የሚመዘግበው የተሽከርካሪው

Facilitation Program Standard;

2/ Any weighing device certified in accordance with the provisions of Sub-Article (1) of this Article shall be calibrated and issued with a certificate of competence at least once in a year as to comply with the relevant Tripartite Transport and Transit Facilitation Program Tripartite functioning of weighing devices;

3/ The calibration and certification of weighing devices stipulated under Sub-Articles (1) and (2) shall be carried out as per the national standards set by a legally authorized body until such time that the standards set by the Tripartite Transport and Transit Facilitation Program become effective;

4/ The weighing station shall keep the certificate attesting the proper functioning of the weighing device.

## 5. **<u>Determination of Weight and Dimension of Vehicles</u>**

1/ Any importer or manufacturer of a motor vehicle shall, before using or cause to be used, have the weight and dimension of such motor vehicle registered at the competent organ in accordance with the provisions of this Regulation;

2/ the Ministry or the legally authorized body shall register the motor vehicle as per Sub-Article (1) of this Article where the weight and dimension of the

Scanned by CamScanner

ክብደት እና መጠን በዚህ ደንብ ከተገለፀው የክብደትና የመጠን ወሰን ካልበለጠ ብቻ ነው፡

፫/ ሚኒስቴሩ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ተሽከርካሪውን ከመመዝገቡ በፊት የተሽከርካሪውን ክብደትና መጠን ወሰን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከተሽከርካሪው አምራች የሚቀርበውን የቴክኒክ መመዘኛ ማንዋል እና ስፔሲፊኬሽን መሠረት ሊያደርግ ይችላል፡

፬/ ለማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ ከተፈቀደው ክብደት ወይም መጠን በላይ የሆነ ተሽከርካሪ በማንኛውም መንገድ ላይ ማሽከርከር ወይም እንዲሽከረከር ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## ፮. የተፈቀደ የተሽከርካሪ መጠን

ማናቸውም ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ ተሳቢ ወይም ግማሽ ተሳቢ ጭነት ቢኖረውም ባይኖረውም፡-

፩/ የተሽከርካሪ፣ የተሳቢ ወይም የግማሽ ተሳቢ ጠቅላላ የጎን ስፋት ከፊት የውጭ በኩል ከቀኝ ጠርዝ እስከ ግራ ጠርዝ ወይም በተቃራኒው ተለክቶ ከ፪ነጥብ፷፭ ሜትር መብለጥ የለበትም፡

፪/ የተሽከርካሪ፣ የተሳቢ ወይም የግማሽ ተሳቢ ጠቅላላ ከመንገድ ከፍታው ጭነቱን ጨምሮ ከ፬ነጥብ፷ ሜትር መብለጥ የለበትም፡

፫/ የማናቸውም ያልተጣመረ ነጠላ ባለሞተር ተሽከርካሪ፣ የፊትና የኋላ መከላከያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ከፊት ጠርዝ እስከ ኋላው ጠርዝ ከ፲፪ነጥብ፶ ሜትር መብለጥ የለበትም፡

motor vehicle does not exceed the limits stipulated in this Regulation;

3/ The Ministry or the legally authorized body may use the technical manuals and specifications of the manufacturer of the motor vehicle in registering the weight and dimension of the motor vehicle as stated under Sub-Article (2) of this Regulation;

4/ It is prohibited for any person to operate or cause the operation of a motor vehicle the weight or dimension of which exceeds the limits determined in this Regulation.

## 6. Permitted Dimension of Vehicles

The total dimension of any motor vehicle, trailer or semi-trailer, loaded or unloaded shall not exceed the following:

1/ Overall outside width of motor vehicle, trailer or semi-trailer measured from front external right edge to left edge or vice versa: 2.65 meters;

2/ Overall height of a vehicle, trailer or semi-trailer: including its load: 4.60 meters from road surface;

3/ Overall length of single motor vehicle (rigid chassis), including the front and rear bumpers: 12.50 meters;

Scanned by CamScanner

፬/ የተጣመረ ተሽከርካሪ ወይም ባለሞተር ተሽከርካሪ ከነተሳቢው የፊትና የኋላ መከላከያዎቹን ጨምሮ ጠቅላላ ርዝመቱ ከፊት ጠርዝ እስከ ኋላው ጠርዝ ከ፲፰ነጥብ፭ ሜትር መብለጥ የለበትም፤

፭/ ማናቸውም ተቀጣይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ጠቅላላ ርዝመት ከ፳፪ ሜትር መብለጥ የለበትም፡፡

**፯. ስለተቀጣይ ተሽከርካሪዎች**

ማናቸውም ተቀጣይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ተቀጣጥለው ለመጓዝ የሚፈቀድላቸው:-

፩/ የሚስበው ተሽከርካሪ እና አንድ ወይም ሁለት ተሳቢዎች፤

፪/ አንድ ተሽከርካሪ ሌላ ተሳቢ ካልሆነ ተሽከርካሪ ጋር ሲቀጠል፤

፫/ በአደጋ ወይም በብልሽት ጊዜ ከአንድ ተሽከርካሪ ጋር ሌላ ተሳቢ ያልሆነ ባለሞተር ተሽከርካሪ እና ተሳቢ ሲቀጠሉ ይሆናል፡፡

**፰. ከተሽከርካሪ አካል ውጭ የሚውል ጭነት**

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው:-

፩/ ለማንኛውም ሰው ጭነቱ ከተሽከርካሪው ፊት እና ከበስተኋላው መጨረሻ ካለው አካሉ ፩ነጥብ፳፭ ሜትር በላይ የሆነ ጭነት የጫነን ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ለማንኛውም ሰው ጭነቱ ከተሽከርካሪው የቀኝ ወይም የግራ ጎን ካለው አካል ፲፭ ሴንቲ ሜትር (ዜሮነጥብ፲፭ ሜትር) በላይ የሆነን ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ማሽከርከር የተከለከለ ነው፡፡

4/ Overall length of articulated vehicle or truck tractor and its trailer, including the front and rear bumpers or load: 18.5 meters;

5/ Overall length of a combination of vehicles: 22 meters.

**7. A Combination of Vehicles**

Any Combination of Vehicles may be allowed to be operated where:

1/ A drawing vehicle with one or two trailers;

2/ A vehicle drawing one other vehicle which is not a trailer;

3/ In the case of an emergency or a malfunction /including damage/, a vehicle drawing another motor vehicle and a trailer.

**8. Projecting Loads**

Without prejudice to the provisions of Article 6 of this Regulation;

1/ A person may not operate on a public road a vehicle on which the load projects to the front or the rear of that vehicle more than 1.25 metre.

2/ A person may not operator on a public road a vehicle on which the load projects to either side of that motor vehicle more than 15 centi metre (0.15 metre).

Scanned by CamScanner

፱. **በመንገድ ላይ እንዲያርፍ የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት**

፩/ በዚህ ደንብ ውስጥ በተለይ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንም ሰው በማንኛውም መንገድ ላይ ክብደቱ በዚህ ደንብ ውስጥ ከተወሰነው በላይ የሆነን ማንኛውንም ተሽከርካሪ መኪና መንዳት ወይም ማንቀሳቀስ፣ ወይም ለተሽከርካሪ መኪናው ባለቤት መኪናው እንዲንቀሳቀስ ወይም ተነድቶ እንዲሄድ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በመንገድ ላይ ባለሞተር ተሽርካሪን ወይም የተቀጣጠሉ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች እንዲያሽከረክር በተለይ የማይፈቀድለት ለተሽከርካሪው በአየር የተሞሉ ጎማዎች የተገጠሙለት እግሮቹ፡-

ሀ) ጎማው ላይ ያለው ክብደት፡-

(፩) በመሪ አክስል ላይ የተገጠመ ከሆነ ከ ፫ሺ.፰፻፶(ሦስት ሺ.ህ ስምንት መቶ ሃምሣ) ኪሎ ግራም የበለጠ፤ ወይም

(፪) ከመሪው አክስል ውጪ የተገጠመ ከሆነ ከ ፬ሺ. (አራት ሺ.ህ) ኪሎ ግራም የበለጠ እንደሆነ ነው፡፡

ለ) የነጠላ አክስል ሁለት ወይም ሶስት ጎማዎች ተገጥመውለት ክብደቱ፡-

(፩) የመሪ አክስል ከ ፯ሺ.፯፻ (ሰባት ሺ.ህ ሰባት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ፣ ወይም

(፪) ከመሪው አክስል ውጪ የተገጠመ ከሆነ ከ ፰ሺ. (ስምንት ሺ.ህ) ኪሎ ግራም የበለጠ እንደሆነ ነው፡፡

9. **Maximum Permissible Mass in Relation to Road Pavement**

1/ Unless authorized with a Special Permit issued as per this Regulation, it shall be prohibited for any person to operate or cause to be operated a motor vehicle the maximum permissible mass of which exceeds those determined in this Regulation.

2/ A person may not operate on a public road a motor vehicle or a combination of motor vehicles, the wheels of which are fitted with pneumatic tyres, if:

a) the wheel mass of wheels:

(1) which are fitted to a steering axle, exceeds 3,850 (Three Thousand Eight Hundred Fifty) kilograms; or

(2) which are fitted to axles other than a steering axle, exceeds 4,000 (Four Thousand) kilograms.

b) the mass of a single axle fitted with two or three wheels:

(1) which is a steering axle, exceeds 7,700 (Seven Thousand Seven Hundred) kilograms; or

(2) other than a steering axle, exceeds 8,000 (Eight Thousand) kilograms;

Scanned by CamScanner

ሐ) አራት ጎማዎች የተገጠሙለት የነጠላ አክስል የአክስል ክብደቱ ፲ሺ (አስር ሺህ) ኪሎ ግራም ሲሆን ነገር ግን አራት ጎማዎች የተገጠሙለት ነጠላ አክስል ከሆነ የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት እና፡-

(፩) የተተወ (የማይፈለግ) ቆሻ አጭቆ ለመጫን እንዲያመች ታስቦ ከተሰራ ተሽከርካሪ ጋር ሲገጠምና ይህንኑ የተተወ ቆሻ ጭኖ በሚሄድበት ጊዜ ከ፲ሺ፪፻ (አስር ሺህ ሁለት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ እንደሆነ፤

(፪) ብልሽት ካለበት ተሽከርካሪ ጋር ከተገጠመ ከ፲ሺ፪፻ (አስር ሺህ ሁለት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ እንደሆነ፤

(፫) የባቡር አውቶቢስ ኋለኛ ወይም መካከለኛ ክፍል ላይ እንዲቀመጥ በሚደረግበት ጊዜ ክብደቱ ከ፲ሺ፪፻ (አስር ሺህ ሁለት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ ሲሆን፤ ሆኖም ፈጣን የባቡር አውቶቢስ ማጓጓዣ ከሆነ የመሪው አክስል ወይም ሌሎች የመሪ አክስል ያልሆኑ አክስሎች የሚፈቀድላቸው ከፍተኛ የክብደት መጠን ፲፫ሺ (አስራ ሦስት ሺህ) ኪሎ ግራም ሆኖ መጓዝ የሚፈቀድላቸውም ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀላቸው መስመር ብቻ ከሆነ፤

(፬) ባቡር አውቶቢስ ባልሆኑ አውቶቢሶች ላይ የተገጠመ ከሆነ ከ፲ሺ፪፻ (አስር ሺህ ሁለት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ ሲሆን፤ ሆኖም ለአንድ ሁኔታ ማከበሪያ አገልግሎት የሚሰጥ ፈጣን አውቶብስ ወይም በመንገድ ላይ በተዘረጋ የኤሌክትሪክ ኃይል

c) the axle mass of a single axle fitted with four wheels is 10,000 (Ten Thousand) kilograms, but the permissible maximum mass for a single axle fitted with four wheels and:

(1) which is fitted to a vehicle designed to compact refuse and which is carrying such refuse, exceeds 10,200 (Ten Thousand Two Hundred) kilograms;

(2) which is fitted to a break down vehicle, exceeds 10,200 (Ten Thousand Two Hundred) kilograms;

(3) which is placed in the rear or middle of a bus-train, exceeds 10,200 (Ten Thousand Two Hundred) kilograms: Provided that in the case of a rapid transport bus-train the maximum permissible mass on the drive axle and the other non-steering axle is 13,000 (ThirteenThousand)kilograms;

(4) which is fitted to a bus, other than a bus-train, exceeds 10, 200 (Ten Thousand Two Hundred) kilograms: Provided that in the case of a rapid transport complementary bus,

Scanned by CamScanner

አማካኝነት የሚነዳ ፈጣን አውቶብስ የሚፈቀድላቸው ከፍተኛ የክብደት መጠን ፲፪ሺ (አስራ ሁለት ሺህ) ኪሎ ግራም ሆኖ መንዝ የሚፈቀድላቸውም ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀላቸው መስመር ብቻ ከሆነ ነው፡፡

መ) አራት ጎማዎች ለተገጠሙለት የጥንድ አክስል የተፈቀደ ከፍተኛ ክብደት፤-

(፩) የመሪ አክስል ክፍል ከ፲፭ሺ፬፻ (አስራ አምስት ሺህ አራት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ እንደሆነ፤ ወይም

(፪) የመሪ ጥንድ አክስል ክፍልን ሳይጨምር ጥንድ አክስል ክፍል ከ፲፮ሺ (አስራ ስድስት ሺህ) ኪሎ ግራም የበለጠ እንደሆነ ነው፡፡

ሠ) ስምንት ጎማዎች ለተገጠሙለት ጥንድ አክስል ክፍል የሚፈቀድላቸው ከፍተኛ የክብደት መጠን ፲፰ሺ (አስራ ስምንት ሺህ) ኪሎ ግራም ያልበለጠ ሆኖ ነገር ግን ለጥንድ አክስል፡-

(፩) ተሳቢውን ሳይጨምር ለተሽከርካሪው ብቻ ሲሆን እና ተሽከርካሪውም የተሰራው የተተወ (የማይፈለግ) ቆሻሻ አጭቆ ለመጫን እንዲያመች ለማድረግ ታስቦ የተሰራና ተሽከርካሪው ይህንኑ የተተወ ቆሻሻ ጭኖ በሚሄድበት ጊዜ ክብደቱ ከ፳ሺ፬፻ (ሃያ ሺህ አራት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ ከሆነ፤

(፪) ከተበላሸ ተሽከርካሪ ጋር ከተገጠመ ከ፳ሺ፬፻ (ሃያ ሺህ አራት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ ከሆነ ነው፡፡

or a rapid transport trunk bus, the maximum permissible mass is 12,000 (Twelve Thousand) kilograms.

d) the maximum permissible mass for a tandem axle fitted with four wheels, and:

(1) which is a steering axle unit, exceeds 15,400 (Fifteen Thousand Four Hundred) kilograms; or

(2) which is a tandem axle unit other than a steering tandem axle unit, exceeds 16,000 (Sixteen Thousand) kilograms.

e) the maximum permissible mass of tandem axle unit fitted with eight wheels, is 18,000 (Eighteen Thousand) kilograms but for a tandem axle:-

(1) which is fitted to a vehicle, except a trailer, designed to compact refuse and which is carrying such refuse, exceeds 20,400 (Twenty Thousand Four Hundered) kilograms;

(2) which is fitted to a breakdown vehicle, exceeds 20,400 (Twenty Thousand Four Hundered) kilograms.

Scanned by CamScanner

ረ) እያንዳንዳቸው አክስሎች ላይ ሁለት ወይም ሶስት ጎማ የተገጠመላቸው ባለ ሶስት አክስል ክፍል ላይ ለእያንዳንዱ አክስል የሚፈቀድ ከፍተኛ ክብደት፡-

(፩) የመሪ አክስል ክፍል ከ፳፫ሺ፩፻ (ሃያ ሦስት ሺህ አንድ መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ፤ ወይም

(፪) ከመሪ አክስል ክፍል በስተቀር ያሉት አክስሎች ክፍል ከ፳፬ሺ (ሃያ አራት ሺህ) ኪሎ ግራም የበለጠ ከሆነ ነው፡፡

ሰ) እያንዳንዳቸው አክስሎች ላይ አራት ጎማ የተገጠመላቸው ባለ ሶስት አክስል ክፍል የሚፈቀድ ከፍተኛ ክብደት ከ፳፬ሺ (ሃያ አራት ሺህ) ኪሎ ግራም የበለጠ፤ እና

ሸ) አንዱ አክስል የመሪ አክስል ሆኖ አራት ጎማዎች ለተገጠሙለት እና ፈጣን ማጓጓዣ አውቶብስ ላይ የተገጠመ ባለሁለት አክስል ክፍል የሚፈቀደው ከፍተኛ ክብደት የሁለቱ አክስሎች ክብደት ድምር ከ፲፰ሺ፪፻ (አስራ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ) ኪሎ ግራም የበለጠ ከሆነ ነው፡፡

፫/ ከላይ የተቀመጠው የመሪ አክስል ወይም የመሪ አክስል ክፍል ወሰን የፈጣን ትራንስፖርት አውቶቢሶችን ወይም የፈጣን ትራንስፖርት ባለባቡር አውቶቢሶች ላይ ለመዞር የሚፈጅባቸውን ርቀት እንዲቀንስ የሚረዱ ሌሎች ማናቸውም አክስሎች ወይም አክስል ክፍል ላይ

f) the maximum permissible mass for a tri-dem axle unit where each axle is fitted with two or three wheels, and:

(1) which is a steering axle unit, exceeds 23,100 (Twenty Three Thousand One Hundred) kilograms; or

(2) which is an axle unit other than a steering axle unit, exceeds 24, 000 (Twenty Four Thousand) kilograms.

g) the maximum permissible mass for a tridem axle unit where each axle is fitted with four wheels, exceeds 24,000 (Twenty Four Thousand) kilograms; and

h) the maximum permissible mass of a tandem axle unit of which one axle is a drive axle with four wheels and the other is an axle with two wheels, and which is fitted to a rapid transport bus, if the sum of the two axle mass loads exceeds 18,200 (Eighteen Thousand Two Hundred) kilograms.

3/ The limitations on steering axles and steering axle units above, do not apply to any axle or axle unit which assists in reducing the turning circle of a rapid transport bus or rapid transport bus-train, but which is not the front

Scanned by CamScanner

ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው መንገድ ላይ ከባለሦስት አክስል በላይ የሆነ አክስል ያለውን ተሽከርካሪ ማሽከርከር አይፈቀድለትም፡፡

## ፲. ከብሪጅ አቅም ጋር በተያያዘ የሚፈቀድ ከፍተኛ ክብደት

፩/ ማንኛውም ሰው መንገድ ላይ ተሽርካሪዎችን ወይም የተቀጣጠሉ ተሽከርካሪዎች በአየር የተሞሉ ጎማዎች የተገጠሙለት ሆኖ ማናቸውም የተሽከርካሪው ወይም የተቀጣጣይ ተሽከርካሪው የአክስል ስብስብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) የተወሰነውን ክብደት በ ፪ሺ፩፻ ተባዝቶ ፲፰ሺ ተደምሮ ከሚገኘው አጠቃላይ የአክስል ክብደት መብለጥ የለበትም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለፀው የአክስል ስብስብ ተከታታይ አክስሎችን የሚያካትት ሆኖ ነጠላ አክስል ብቻውን ከሆነ ግን አያካትተውም፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለፀው መጠን በሜትር የሚለካ ሆኖ ከየትኛውም የአክስሎች ስብስብ የመጀመሪያው የአክስል ማዕከል ጀምሮ የዚሁ አክስል ስብስብ የመጨረሻ ማእከል ድረስ በአስረኛ ሜትር የሚለካ ነው፡፡

፬/ የተለካው መጠን እርግጠኛ የሆነ የሜትር እና በ፲ኛ የሜትር ልኬት ካልሆነ ቀጣዩ ከፍተኛ በ፲ የሚለካ የሜትር ልኬት ከልኬቱ በልጦ በሚገኝበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተገለጸውን መጠን ለማስላት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

axle or front axle unit.

4/ A person may not operate on a public road a vehicle fitted with an axle exceeding a tridem axle unit.

## 10. Maximum Permissible Mass in Relation to the Carrying Capacity of Bridges

1/ A person may not operate on a public road a vehicle or combination of vehicles, the wheels of which are fitted with pneumatic tyres, if the total axle mass of any group of axles of such vehicle or combination of vehicles exceeds the mass in kilograms determined by multiplying the dimension of such group measured as referred to in Sub-Article (3) of this Article by 2,100 and adding 18, 000.

2/ A group of axles referred to in Sub-Article (1) of this Article may comprise any series of axles but may not consist of one axle unit alone.

3/ The dimension referred to in Sub-Article (1) of this Article must be measured in metre and tenths of a metre from the centre of the first axle of any group of axles to the centre of the last axle of such group.

4/ If the dimension so measured is not a definite figure in metre and tenths of a metre, the next highest number in tenths of a metre with which the dimension so measured is exceeded must be used for the calculation referred to in Sub-Article (1) of this Article.

Scanned by CamScanner

፭/ የተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች የአክስል ስብስብ በሚለካ ጊዜ የዚሁ ተቀጣጣይ ተሽከርካሪ በቅደም ተከተል መስመር የሚለኩ እና የእነዚህ ተቀጣጣይ ተሽከርካረዎች ሁለቱም ጎኖች መለካት አለባቸው፣ የሁለቱም ጎኖች ልኬት የሚለያይ ከሆነ ረጅም ልኬት ያለው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ላይ የተገለጸውን ለማስላት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

፮/ የሚፈቀድ የትርፍ ክብደትን በሚመለከት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፲፩. ለተሽከርካሪዎች ወይም ለተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች የሚፈቀደው ከፍተኛ ክብደት

ለተሽከርካሪዎች፣ ለተቀጣጣይ ተሽከርካሪዎች ወይም በዝርዝሩ ውስጥ ለተካተቱ ተሽከርካሪዎች የሚፈቀደው ከፍተኛ ክብደት ከሚከተሉት ትንሹን ይሆናል፡-

፩/ ከፍተኛ የተፈቀደ የአክስል ወይም የአክስል ክፍል ክብደት ድምር፣

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፱ መሠረት የሚወሰን ከፍተኛው የተፈቀደ ክብደት፣ ወይም

፫/ ፶፮ ቶን ነው፡፡

## ፲፪. ተሽከርካሪን ስለመያዝ

በሌላ ሕግ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም የተሽከርካሪ ክብደትን በሚመለከት በዚህ ደንብ ከተቀመጠው ጠቅላላ ክብደት በላይ የሆነ ተሽከርካሪ ወይም ተጣማሪ ተሽከርካሪ ከመጠን በላይ የሆነውን

5/ Where a group of axles of a combination of vehicles is measured, the vehicles of such combination must be positioned in line and both sides of such combination of vehicles must be measured, and if the dimensions of the two sides differ, the longer dimension must be used for the calculation referred to in Sub-Article (1) of this Article.

6/ The Ministry may determine the tolerance level to be allowed for mass exceeding the permitted level in this Article through a Directive to be issued by it.

## 11. Maximum Permissible Mass for a Vehicle or a Combination of Vehicles

The maximum permissible mass for a vehicle or a combination or vehicles is the least of:

1/ The sum of the maximum permissible axle and axle unit masses;

2/ The maximum permissible mass determined in terms of Article 9 of this Regulation ; or

3/ 56 tonnes.

## 12. Detaining Vehicle

Notwithstanding any provision to the contrary, a vehicle or combination of vehicles that is found to be of a mass in excess of the legal load limit, may be detained until the load of that vehicle or

Scanned by CamScanner

ጭነት እስኪያስተካክል ወይም ወደሌላ ተሽከርካሪ እስኪቀንስ ድረስ ተሽከርካሪው ተይዞ ሊቆይ (ሊታገድ) ይችላል፡፡

፲፫. <u>ስለ ኃላፊነት</u>

፩/ የተጣመሩ ተሽከርካሪዎች ባለቤቶች የተለያዩ ሆነው ሲገኙ በዚህ ደንብ የተቀመጠውን ቅጣት የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የጎታች ባለሞተር ተሽከርካሪው ባለቤት ነው፡፡

፪/ በኮንቴነር የሚጓጓዝ ጭነት ስለክብደት ወይም ስለመጠን ወይም ለሁለቱም በዚህ ደንብ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች ተላልፎ ከተገኘ በዚህ ደንብ የተቀመጠውን ቅጣት የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የጭነቱ ባለቤት ነው፡፡

፫/ መጠኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ከተፈቀደው በላይ ሆኖ ለተገኘ ተሽከርካሪ በዚህ ደንብ የተቀመጠውን ቅጣት የመክፈል ኃላፊነት ያለበት የተሽከርካሪው ባለቤት ነው፡፡

፬/ አክስሉ ወደ ላይ ተነስቶ የተገኘ ተሽከርካሪን ያሽከረከረ አሽከርካሪ በዚህ ደንብ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ድንጋጌን በመተላለፍ አክስሉ ተነስቶ የተገኘ ተሽከርካሪ አክስሉ ዝቅ ሲደረግ በተሽከርካሪው ላይ ትርፍ ጭነት የተገኘበት እንደሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት በዚህ ደንብ መሠረት የሚጣልበትን ቅጣት አያስቀርም፡፡

combination of vehicles is rectified or offloaded onto another vehicle before the vehicle concerned may be released.

13. **<u>Persons Liable</u>**

1/ For the purpose of this Regulation, where different operators or owners are registered for different vehicles in a combination of vehicles, the owner registered for the truck tractor of that combination of vehicles is liable for penalties stipulated in this Regulation in relation to that combination of vehicles.

2/ Where the load is a container and the actual mass exceeds the mass indicated in the Bill of Lading, the owner of the container shall be held liable and pay the penalty stated in this Regulation.

3/ The owner of a vehicle shall pay the penalty stated in this Regulation where his vehicle's dimension exceeds the limits stipulated under Article 6 of this Regulation.

4/ Where a driver is found driving a vehicle the axle of which is lifted, he shall pay the penalties stated in this Regulation.

5/ The owner of the vehicle shall pay the penalty stated in this Regulation where when the lifted axle as per Sub-Article (4) of this Article is put back to its original position; and the mass of that vehicle is found exceeding the limit stipulated in this Regulation.

Scanned by CamScanner

፮/ ማንኛውም ተሽከርካሪው ትርፍ ጭነት ቢጭንም ባይጭንም የሚዛን ጣቢያ ውስጥ ገብቶ መመዘን ሲገባው ለማስመዘን ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም ሚዛን ጣቢያዎችን አልፎ የሄደ ወይም ለመሄድ የሞከረ እንደሆነ አሽከርካሪው በዚህ ደንብ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ ይከፍላል፡፡

፯/ አንድ ተሽከርካሪ በአንድ ጊዜ ለመጠንም ሆነ ለጭነት የተቀመጠውን ልክ ተላልፎ ከተገኘ ከሁለቱ ቅጣቶች ከፍ ያለውን ብቻ ይቀጣል፡፡

፰/ በዚህ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱት ቅጣቶች በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ መሠረት የሚጣሉ ቅጣቶችን አያስቀሩም፡፡

## ፲፬. <u>የቅጣት መጠን</u>

፩/ ከተፈቀደው ክብደት በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች የሚከፍሉት ቅጣት በዚህ ደንብ አባሪ አንድ ላይ የተዘረዘረ ሲሆን ይህ ቅጣት በየዓመቱ በመደበኛ አክስል በኪሎ ሜትር ያለውን ወጪ በማስላት ይከለሳል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ ከተፈቀደው የበለጠ መጠን ያለው ተሽከርካሪን ማሽከርከር ብር ፭ሺ (አምስት ሺህ) ያስቀጣል፡፡ በዚህ ደንብ ስለመጠን የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ተላልፎ የተገኘ ተሽከርካሪ መጠኑን በዚህ ደንብ በተፈቀደው መሰረት እስኪያስተካክል ድረስ ሰሌዳው እና ሌሎች መለያዎቹ ይያዛሉ፡፡

6/ Whether loaded or unloaded the driver of a vehicle who evades or attempts to evade a weigh station shall pay the penalty stipulated in this Regulation.

7/ When a vehicle is found concurrently violating both the axle load and the dimension limit specified in this Regulation, only the highest penalty shall be imposed.

8/ The penalties imposed in accordance with this Regulation shall not relieve of any other penalty under the Road Transport Traffic Control Regulation.

## 14. <u>Penalties</u>

1/ The penalties imposed for overload are as listed in Annex One to this Regulation; and must be reviewed annually in terms of the cost of an Equivalent Standard Axle/kilometre.

2/ Operating a vehicle with a dimension exceeding the limit stated under this Regulation shall entail a penalty of ETB 5,000(Five Thousands). The vehicle so found in violation of the provisions of this Regulation shall be confiscated of its plate and other vehicle identifications until such time that it rectifies its dimension in accordance with this Regulation.

Scanned by CamScanner

፫/ በዚህ ደንብ የተቀመጡት ቅጣቶች በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ መከፈል አለባቸው፡፡ ቅጣቱ በ፯ የሥራ ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ የተሽከርካሪው ባለቤት፣

ሀ) በቀጣይ ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ በመጀመሪያ የተጣለውን ቅጣት ላይ ፳ በመቶ ተጨማሪ ቅጣት ይከፍላል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) በተቀመጠው ጊዜ ካልከፈለ በቀጣይ ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ በመጀመሪያ የተጣለውን ቅጣት ላይ ፶ በመቶ ተጨማሪ ቅጣት ይከፍላል፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ለ) በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ካልከፈለ በመጀመሪያ የተጣለውን ቅጣት እጥፍ ይከፍላል፡፡

፬/ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በወቅቱ ያልተከፈሉ ቅጣቶችና እና ቀሪ ተጨማሪ ቅጣቶችን በሚመለከት መረጃ መያዝ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሐ) መሠረት የተጣለው ቅጣት በ፴ የሥራ ቀናት ያልተከፈለ ከሆነ ተሽከርካሪው እንዳይንቀሳቀስ የሚከለከል ሲሆን ቅጣቱም በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ መሰረት እንዲሰበሰብ ሊደረግ ይችላል፡፡

3/ The penalties imposed under this Regulation must be paid within seven working days. Where the penalties have not been paid within the 7 working days, the owner of the vehicle shall;

a) Pay additional penalty of 20 percent of the penalty within 15 working days exceeding the initial seven working days period.

b) Pay additional penalty of 50 percent of the penalty within the next 15 working days, where the owner fails to observe the penalty period stated under this Sub-Article (3) paragraph (a).

c) Pay additional penalty of 100 percent of the penalty where the owner did not comply with the payment period stated under this Sub-Article (3) paragraph (b).

4/ The competent authority must keep record of late payments and the additional penalties to be paid in terms of outstanding penalties.

5/ Where the penalty imposed under Sub-Article (3) paragraph (c) of this Article has not been paid within 30 working days, the vehicle so penalized shall not be allowed to operate and the penalty may be collected in accordance with the Ethiopian Civil Code.

Scanned by CamScanner

፮/ ማንኛውም ተሽከርካሪ ጭነት በጫኔ ጊዜ አክስሉን ወደ ላይ ማንሳት የማይቻል ሲሆን ጭነት በጫነ ጊዜ አክስሉ ወደ ላይ ተነስቶ ከተገኘ አክስሉ ወደታች ዝቅ እንዲል ተደርጎ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ) ያስቀጣል፡፡

፯/ ማንኛውም ተሽከርካሪ ትርፍ ጭነት ቢጭንም ባይጭንም የሚዛን ጣቢያ ውስጥ ገብቶ መመዘን በሚገባ ጊዜ ሁሉ ሳይመዘን ጣቢያውን አልፎ ቢገኝ ብር ፪ሺ (ሁለት ሺህ) ያስቀጣል፡፡

## ፲፭. ሌሎች ቅጣቶች

በዚህ ደንብ የተደነገጉትን የክብደት እና መጠን ወሰን እንዲሁም ሌሎች ክልከላዎችን በመተላለፍ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣል ቅጣት በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር ፪፻፰/፪ሺ፲፩ እና የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ /ማሻሻያ/ ቁጥር ፫፻፺፭/፪ሺ፱ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የሚጣሉ ቅጣቶችን አያስቀርም፡፡

## ፲፮. የተፈቀደ ክብደትን ስለመቀነስና ምልክቶችን ስለመትከል

፩/ በዚህ ደንብ የተፈቀደው የጭነት ክብደት በመንገዶች ላይ ጉዳት የሚያመጣ ሆኖ ሲገኝ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ተለይተው በተገለፁት መንገዶች ወይም የመንገድ ክፍሎች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ለተወሰነ ጊዜ የሚፈቀደውን ጠቅላላ ክብደት የመቀነስ ሥልጣን አለው፡፡ ይሁንና በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የሚቀነሰውን የክብደት መጠንና የሚቆይበትን ጊዜ እንደየሁኔታው ይወስናል፡፡

6/ A vehicle may not be operated with a lifted axle while loaded; where a vehicle is so found a penalty of ETB 2,000 (Two Thousand Birr) shall be imposed and the axle shall be put back to its original position.

7/ Where any vehicle loaded or unloaded is found disregarding weighing stations while it is required so, a penalty of ETB 2,000 (Two Thousand Birr) shall be imposed.

## 15. Other Penalties

The penalties stipulated in this Regulation regarding weight, dimension or any other stipulation of the Regulation shall not relieve from other penalties imposed by the Road Transport Traffic Control Council of Ministers Regulations No. 208/2011 and Road Transport Traffic Control Council of Ministers Regulation (Amendment) No 395/2017.

## 16. Reduction of Mass and Signs Installation

1/ The competent authority may, order the mass of vehicles permitted in this Regulation to be lowered or reduced, where the safety of the roads so dictates, to a lesser level in the specified roads or parts of roads where necessary for specified time period. However, in such instances, the mass to be reduced and the duration such decision may remain in force shall be determined by the competent authority on a case by case basis.

Scanned by CamScanner

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) በተመለከተው መሠረት ማናቸውም የክብደት መቀነስ ወይም መወሰን በተደረገ ጊዜ ውሳኔው በሚነካቸው መንገዶች ላይ የሚመለከተው አካል ምልክቶችን ይተክላል፡፡

**፲፯. ልዩ ፈቃድ**

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ ደንብ ከተወሰነው በላይ የሆነ ክብደት ያለው ተሽከርካሪ መንገዶችን አደጋ ላይ ሊጥል በማይችል መልኩ በአንድ የመንገድ መስመር ላይ ለመጓዝ እንዲችል አስፈላጊና ትክክል መስሎ በሚታየው አኳኋን ልዩ ፈቃድ ለመስጠት ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ጥያቄ ሲቀርብለት በዚህ ደንብ ከተወሰነው የተሽከርካሪ መጠን በላይ የሆነ መጠን ያለው ተሽከርካሪ መንገዶችን አደጋ ላይ ሊጥል በማይችል መልኩ እና የትራፊክ ፍሰትን ሊያስተጓጉል በማይችል መልኩ በአንድ የመንገድ መስመር ላይ ለመጓዝ እንዲችል አስፈላጊና ትክክል መስሎ በሚታየው አኳኋን ልዩ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፫/ ልዩ ፈቃድ የሚሰጠው ለአንድ ተሽከርካሪ ወይም በጣምራ ለሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ለአንድ ጉዞ ብቻ ነው፡፡

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት የሚሰጠው ልዩ ፈቃድ ለመንገዶች ደህንነት ሲባል በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ Where an order is issued as per Sub-Article (1) of this Article, visible signs to this effect shall be installed in the roads the order affects.

**17. Special Permit**

1/ The Ministry or the competent authority may, when requested, issue abnormal load or vehicle permit in relation to a vehicle exceeding the mass limits permitted in this Regulation to use specified roads in ways it thinks suitable where such permission may not put such specified roads at risk.

2/ The Ministry may, when requested, issue special permit to vehicles exceeding the dimension limits permitted in this Regulation to use specified roads in ways it thinks appropriate where such permission may not put such specified roads at risk or hamper road traffic.

3/ An abnormal load or vehicle permit is valid only for the vehicle specified or a convoy thereof and for a single trip only.

4/ Where the safety of roads or safety of transport so requires, the Ministry may attach specific conditions to the permits to be issued as per Sub-Article (2) and (3) of this Article, respectively.

Scanned by CamScanner

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ለተሽከርካሪው የሚሰጠው ልዩ ፈቃድ የተሽከርካሪውን አክስሎች ክብደት ወይም የተሽከርካሪውን ጠቅላላ ክብደት፣ ጭነቱን፣ አጃቢ (እንደ አስፈላጊነቱ)፣ የማስጠንቀቂያ መብራትና መሳሪያ መጠቀምን፣ ጉዞው የሚከናወንበትን መስመርና ጊዜ፣ እንዲሁም ጭነቱ የመንገድና የአካባቢ ደህንነት በተጠበቀበት ሁኔታ ለማጓጓዝ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

5/ The abnormal load or vehicle permit to be issued as per Sub-Article (2) of this Article shall contain, the axle loads or gross weight; the cargo; escorts (where applicable); hazard light and tools; the trip time; route; and any other details necessary for the safety of the roads and the trip.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) መሠረት ለተሽከርካሪው የሚሰጠው ልዩ ፈቃድ የተሽከርካሪውን እና የጭነቱን መጠን፣ አጃቢ (እንደአስፈላጊነቱ)፣ የማስጠንቀቂያ መብራትና መሳሪያ መጠቀምን፣ ጉዞው የሚከናወንበትን መስመርና ጊዜ፣ እንዲሁም ጭነቱ የመንገድና የአካባቢ ደህንነት በተጠበቀበት ሁኔታ ለማጓጓዝ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

6/ The abnormal load or vehicle permit to be issue as per Sub-Article (3) of this Article shall contain, the dimension of the vehicle and the cargo; escorts (where applicable); hazard light and tools; the trip time; route; and any other details necessary for the safety of the roads and the environment.

፯/ ልዩ ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ በጽሁፍ፣ በፋክስ ወይም በኢሜል የሚቀርብ ሲሆን በውስጡም የጭነቱ አስፈላጊነት፣ የተሽከርካሪውን መጠን፣ የጭነት ክብደት፣ የጭነቱን ስፋት ርዝመት እና ከፍታ፣ የሚጓዝበትን መንገድ፣ የሚጓጓዝበት ተሽከርካሪ፣ የአክስል ብዛትና አቀማመጥ፣ የተሽከርካሪውን ባለቤት፣ የአሽከርካሪውን ሙሉ ስም፣ የጭነቱን አይነት፣ የሚንቀሳቀስ አካልና ሌሎች ሚኒስቴሩ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች መያዝ አለበት፡፡

7/ Application for an abnormal load or vehicle permit may be made through written application, fax or email; and shall contain the reasons for such permit; dimension of the vehicle and load; the proposed route including departure and destination; and its axle load and number; the owner of the vehicle, the driver's full name, details of the cargo and any other specifics as may be required by the Ministry.

Scanned by CamScanner

፰/ የተሰጠው ልዩ ፍቃድ በጉዞ ጊዜ ከተሽከርካሪው ጋር መኖር ያለበት ሲሆን ማንኛውም የሚኒስቴሩ ተቆጣጣሪ ወይም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ወይም ትራፊክ ፖሊስ በጠየቀ ጊዜ መቅረብ አለበት፡፡

፱/ ሚኒስቴሩ በልዩ ፈቃዱ መሠረት መሟላት የሚኖርበት ቅድመ-ሁኔታ ሳይሟላ የቀረ ወይም ተሽከርካሪው በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት እየተሽከረከረ እንዳልሆነ ከተረዳ ልዩ ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል፡፡

፲፰. <u>ቁጥጥር ስለማድረግ</u>

፩/ ሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ የሚወከል አካል የማናቸውም ተሽከርካሪ ክብደት ወይም መጠን በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት መሆኑን ለመቆጣጠር ተሽከርካሪውን የመመርመር ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡

፪/ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሚዛኖችንና ሌሎች ክብደትን ለመመዘን የሚያስችሉ መሳሪያዎችን በመንገድ ላይ በመትከልና በትራፊክ ምልክቶች አማካኝነት በማመላከት የማናቸውም ተሽከርካሪ አክስል ክብደት እና ጠቅላላ ክብደት በዚህ ደንብ በተፈቀደው መሠረት መሆኑን ለመቆጣጠር የመመዘን እና አስፈላጊ የሆኑ በዚህ ደንብ የተደነገጉ ሌሎች ተግባራትን ይፈጽማል፡፡

፫/ በዚህ ደንብ መሠረት ሚኒስቴሩ፣ በሚኒስቴሩ የተወከለ አካል፣ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ወይም ፖሊስ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ያለመፈጸም ጥፋት ሲሆን ትዕዛዙ እስኪፈጸም ድረስ ተሽከርካሪው ወይም ጭነቱ

8/ The abnormal load or vehicle permit so issued shall always remain with the vehicle during the trip and shall be produced when requested so by officers of the Ministry or the competent authority or a traffic police officer.

9/ The Ministry may, cancel the abnormal load or vehicle permit issued as per this Regulation where it finds that the vehicle failed to observe the conditions attached to the permit or where the vehicle is not observing any other directions set in the permit.

18. **<u>Inspection</u>**

1/ The Ministry or its delegate has the power to inspect any vehicle at any time to ensure that vehicle observe the mass or dimension limits permitted in this Regulation.

2/ The competent authority shall be responsible for, by setting up weigh stations; weighing devices and installing signs, inspecting the axle loads, gross mass and other specifications of the vehicles to ensure that they observe the limits permitted in this Regulation.

3/ Failing to observe orders or directions given by the Ministry, the competent authority or police in accordance with this Regulation is an offense; and the Ministry may detain the vehicle or combination of vehicles concerned

Scanned by CamScanner

በተሽከርካሪው ባለቤት ኃላፊነት ተይዞ ይቆያል፡፡

## ፲፱. የመለካት ሥርዓት

፩/ ማንኛውም አሽከርካሪ ተሽከርካሪውን እንዲያስመዝን ሲጠየቅ ማስመዘን አለበት፡፡

፪/ ተሽከርካሪው ሲመዘን የተሽከርካሪው የአክስልና ጠቅላላ ክብደት በሕግ በተቀመጠው መሠረት ሆኖ ከተገኘ የሚዛን ጣቢያው ለአሽከርካሪው የሚዛን ሰርቲፊኬት መስጠት ያለበት ሲሆን ይህም ሰርቲፊኬት የተሽከርካሪውን አክስሎችና ክብደት በተመለከተ እንደይለፍ ያገለግለዋል፡፡

፫/ በተሽከርካሪው ላይ ትርፍ ጭነት በተገኘ ጊዜ፡-

ሀ) በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ከሚዛኑ የተሽከርካሪውን ወይም ተጣማሪ ተሽከርካሪውን ክብደት የሚያሳይ ሰነድ ያዘጋጃል፡፡

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት በተዘጋጀው ሰነድ ላይ ጭነቱ በአግባቡ መመዘኑንና በሰነዱ ላይ የተቀመጠው ንባብ በሚዛኑ ላይ ከተመዘገበው ጋር ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ አሽከርካሪው ይፈርማል፡፡

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ለ) መሠረት አሽከርካሪው በሰነዱ ላይ ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ቅጣቱን ከማስከፈል አያግደውም፡፡

until such time that it observes the orders or directions.

## 19. Weighing Procedure

1/ Any driver shall have the duty, when so instructed, to make the vehicle he is driving weighed by a weighing device.

2/ Upon weighing, where the axles and gross mass of the vehicle is as stipulated in this Regulation, the Weigh Station shall issue a weighbridge certificate which constitutes proof regarding axle and mass only.

3/ Where the vehicle is found with excess load:

a) The competent authority shall issue a document showing the mass of the vehicle or combination of vehicles as weighed.

b) The document so produced as per Sub-Article (3) paragraph (a) of this Article shall be signed by the driver to the effect that the vehicle is properly weighed and that the reading on the notice is the reading shown on the weighing device.

c) Unwillingness of the driver to sign on the record as provided under Sub-Article (3) paragraph (b) of this Article shall not prohibit the competent uthority from enforcing the penalty.

Scanned by CamScanner

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው ቢኖርም፡-

ሀ) ተሽከርካሪው ተጨማሪ ጭነት ያለመጫኑን ለማረጋገጥ በየትኛውም ሚዛን ጣቢያ ወይም ተንቀሳቃሽ ሚዛን እንዲመዘን ሊጠየቅ ይችላል፡፡

ለ) ተሽከርካሪው በድጋሚ በሚመዘንበት ወቅት ክብደቱ ከቀድሞው ንባብ ልዩነት ያለው ሆኖ ከተገኘ የድጋሚው ንባብ ውጤት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## ፳. ቅጣትን የማስከፈል ሥርዓት

፩/ አንድ ተሽከርካሪ በዚህ ደንብ ከተፈቀደው የተሽከርካሪ መጠን በላይ ሆኖ ከተገኘ ሚኒስቴሩ ወይም በሚኒስቴሩ የተወከለ አካል በደንቡ ላይ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ የማስከፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

፪/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፯ መሠረት የሚዘጋጀው የሚዛን ንባብ ትርፍ ጭነትን ለመለየትና በዚህ ደንብ መሠረት የተቀመጠውን ክፍያ ለማስከፈል መሠረት ይሆናል፡፡

፫/ አንድ ተሽከርካሪ ወይም ተጣማሪ ተሽከርካሪ በዚህ ደንብ ከተፈቀደው ጠቅላላ ክብደት በላይ ሆኖ ከተገኘ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በደንቡ ላይ የተቀመጠውን የቅጣት ክፍያ የማስከፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

፬/ አሽከርካሪው በሚዛን ንባቡ ሰነድ ላይ የተመለከተውን ከክብደት በላይ ጭነት እንዲሁም የቅጣት መጠን ለተሽከርካሪው ባለቤት የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ለተሽከርካሪው የተሰጠው ንባብ ለአሽከርካሪው ባለቤት እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article:

a) The vehicle may be required to be weighed at any other Weigh Station to ensure that it does not subsequently carry additional loads after the preceding Weigh Station.

b) Where the vehicle is found with a different reading from the preceding Station, the latest reading prevails.

## 20. Procedure of Penalty Payment

1/ Where a vehicle is found to have exceeded the dimension limit specified in this Regulation, the Ministry or its delegate shall have the responsibility to enforce the penalties imposed as per this Regulation.

2/ The readings of a weighing device produced as per Article 17 of this Regulation shall serve as evidence for identifying excess loads and imposing overload penalties.

3/ Where a vehicle or combination of vehicles is found to be exceeding its maximum permissible mass, the competent authority shall have the responsibility to enforce the penalties imposed as per this Regulation.

4/ The driver is responsible to notify to the owner of the vehicle regarding the overload and the corresponding overload penalty. The reading served to the driver shall be deemed to have been served to the owner of the vehicle.

Scanned by CamScanner

፭/ በዚህ ደንብ የተወሰነውን ክብደት ተላልፎ የተገኘ የተሽከርካሪ ባለቤት፡-

ሀ) በዚህ ደንብ የተመለከተውን ቅጣት ፈጽሞ በትርፍ የተያዘውን ጭነት ያራግፋል፤

ለ) የትርፍ ጭነቱን ማራገፊያ፣ ማስጫኛ እና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችን የተሽከርካሪው ባለቤት ይሸፍናል፤

ሐ) በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ለተሽከርካሪውም ሆነ ለሚራገፈው ጭነት ምንም ዓይነት ኃላፊነት አይኖርበትም፡፡

፮/ በዚህ ደንብ ላይ የተሽከርካሪ ክብደትን በመተላለፍ ለተቀመጡት ቅጣቶች የሚከፈል ክፍያ ለኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሚከፈል ሲሆን የተሽከርካሪ መጠንን በመተላለፍ ለተቀመጡት ቅጣቶች የሚከፈል ክፍያ ለሚኒስቴሩ ይከፈላል፡፡

## ፳፩. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ስለተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና ልክ መወሰኛ ደንብ ቁጥር ፪፻፷፩/፲፱፻፶፭፣ የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና ልክ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፪፻፺፪/፲፱፻፶፯ እና የተሽከርካሪ መኪናዎች ክብደትና መጠን መወሰኛ ማሻሻያ ደንብ ቁጥር ፲፩/፲፱፻፹፪ በዚህ ደንብ ተሽረዋል፡፡

5/ The owner of a vehicle or combination of vehicles found to have exceeded the maximum permissible mass specified in this Regulation:

a) Shall pay the penalties imposed in accordance with this Regulation and shall unload the excess cargo;

b) Shall bear the cost of offloading the excess load, reloading or any other expenses associated therewith;

c) The competent authority shall not be responsible for the offloaded cargo or the vehicle.

6/ The penalties to be paid for violation of maximum permissible mass as stated in this Regulation shall be paid to the Ethiopian Roads Administration; while the penalties to be paid for violation of dimension limit as stated in this Regulation shall be paid to the Ministry.

## 21. <u>Repealed Laws</u>

The Vehicle Size and Weight Regulations No. 261/1962, Vehicle Size and Weight Amendment Regulation No. 292/1964 and Vehicle Size and Weight Amendment Regulation No. 11/1990 are hereby repealed and replaced by this Regulation.

Scanned by CamScanner

**፳፪. <u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፳፫. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>**

ከዚህ ደንብ መጽናት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የገቡና በዚህ ደንብ ስለ ክብደት እና መጠን የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ተላልፈው የተገኙ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**፳፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፴ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**22. <u>Inapplicable Laws</u>**

Any law or practice contradictory to this Regulation shall not be applicable to matters covered under this Regulation.

**23. <u>Transitional Provisions</u>**

Vehicles which entered into the territory of Ethiopia prior to the coming into force of this Regulation and contravening the provisions of this Regulation shall be handled in accordance with Directive to be issued to this effect by the Ministry.

**24. <u>Effective Date</u>**

This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 9th Day of March, 2022.**

**ABIY AHMED (DR.)**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

Scanned by CamScanner

## አባሪ 1 - ትርፍ ጭነት ሲገኝ የሚጣለው ቅጣት

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ እና ፱ ላይ ከተደነገገው አክስል ክብደት በላይ ትርፍ ጭነት ሲገኝ የሚጣለው ቅጣት በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ በሰፈረው መሰረት ይሆናል፡፡

| ከተደነገገው አክስል ክብደት በላይ ትርፍ ጭነት ሲገኝ የሚጣለው ቅጣት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግብሃት | ርቀት (ኪ.ሜ.) | ESA/ ኪ.ሜ. (ብር) | የጥሰት ውጤት | n-VALUE |
| VARIABLES | 300 | 1,21 | 6 | 4 |
| አክስል | መሪ አክስል | የሚነዳ ነጠላ አክስል | ጥንድ አክስል | ባለሶስት አክስል |
| | የተፈቀደ ክብደት=8ቶን | የተፈቀደ ክብደት=10ቶን | የተፈቀደ ክብደት=18ቶን | የተፈቀደ ክብደት=24ቶን |
| | የተፈቀደ ESA=2.16 | የተፈቀደ ESA=1.45 | የተፈቀደ ESA=3.93 | የተፈቀደ ESA=3.68 |
| ትርፍ ጭነት (ኪ.ግ.) | የሚጣል ቅጣት መጠን (ብር) | | | |
| 400 | 1010 | 603 | 794 | 7054 |
| 800 | 2179 | 1285 | 1634 | 8066 |
| 1200 | 3519 | 2056 | 2530 | 9129 |
| 1600 | 5045 | 2924 | 3484 | 10244 |
| 2000 | 6774 | 3895 | 4497 | 11412 |
| 2400 | 8724 | 4978 | 5573 | 12636 |
| 2800 | 10912 | 6182 | 6715 | 13916 |
| 3200 | 13357 | 7514 | 7924 | 15255 |
| 3600 | 16079 | 8984 | 9204 | 16654 |
| 4000 | 19097 | 10601 | 10557 | 18116 |

Scanned by CamScanner

| ከተደነገገው አክስል ክብደት በላይ ትርፍ ጭነት ሲገኝ የሚጣለው ቅጣት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ግብዓት | ርቀት (ኪ.ሜ.) | ESA/ ኪ.ሜ. (ብር) | የጥሰት ውጤት | n-VALUE |
| VARIABLES | 300 | 1,21 | 6 | 4 |
| አክስል | መሪ አክስል | የሚነዳ ነጠላ አክስል | ጥንድ አክስል | ባለሶስት አክስል |
| | የተፈቀደ ክብደት=8ቶን | የተፈቀደ ክብደት=10ቶን | የተፈቀደ ክብደት=18ቶን | የተፈቀደ ክብደት=24ቶን |
| | የተፈቀደ ESA=2.16 | የተፈቀደ ESA=1.45 | የተፈቀደ ESA=3.93 | የተፈቀደ ESA=3.68 |
| ትርፍ ጭነት (ኪ.ግ.) | ትርፍ ጭነት (ኪ.ግ.) የሚጣል ቅጣት መጠን (ብር) | | | |
| 4400 | 22433 | 12374 | 11985 | 19641 |
| 4800 | 26108 | 14313 | 13493 | 21232 |
| 5200 | 30144 | 16428 | 15081 | 22891 |
| 5600 | 34563 | 18730 | 16755 | 24620 |
| 6000 | 39391 | 21229 | 18515 | 26420 |
| 6400 | 44651 | 23937 | 20365 | 28294 |
| 6800 | 50367 | 26863 | 22309 | 30243 |
| 7200 | 56567 | 30021 | 24350 | 32269 |
| 7600 | 63275 | 33421 | 26489 | 34375 |
| 8000 | 70520 | 37076 | 28732 | 36563 |

Scanned by CamScanner

**Annex 1. PENALTIES FOR EXCEEDING PERMISSIBLE AXLE OR AXLE UNIT MASS**

| PENALTIES FOR EXCEEDING PERMISSIBLE AXLE OR AXLE UNIT MASS | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **INPUT** | **DISTANCE (km)** | **ESA/ km (ET Bir)** | **OFFENCE FACTOR** | **n-VALUE** |
| **VARIABLES** | **300** | **1,21** | **6** | **4** |
| **AXLE** | **Steering Axle** | **Single(Drive)Axle** | **Tandem Axle Unit** | **Tridem Axle Unit** |
| **CONFIGURATION** | **Legal Mass=8t** | **Legal Mass=10t** | **Legal Mass=18t** | **Legal Mass=24t** |
| | **Legal ESA=2.16** | **Legal ESA=1.45** | **Legal ESA=3.93** | **Legal ESA=3.68** |
| **OVERLOAD (kg)** | **OVERLOAD FEE (ETB)** | | | |
| **400** | 1010 | 603 | 794 | 7054 |
| **800** | 2179 | 1285 | 1634 | 8066 |
| **1200** | 3519 | 2056 | 2530 | 9129 |
| **1600** | 5045 | 2924 | 3484 | 10244 |
| **2000** | 6774 | 3895 | 4497 | 11412 |
| **2400** | 8724 | 4978 | 5573 | 12636 |
| **2800** | 10912 | 6182 | 6715 | 13916 |
| **3200** | 13357 | 7514 | 7924 | 15255 |
| **3600** | 16079 | 8984 | 9204 | 16654 |
| **4000** | 19097 | 10601 | 10557 | 18116 |
| **4400** | 22433 | 12374 | 11985 | 19641 |
| **4800** | 26108 | 14313 | 13493 | 21232 |

Scanned by CamScanner

| PENALTIES FOR EXCEEDING PERMISSIBLE AXLE OR AXLE UNIT MASS | | | | |
|---|---|---|---|---|
| INPUT | DISTANCE (km) | ESA/ km (ET Bir) | OFFENCE FACTOR | n-VALUE |
| VARIABLES | 300 | 1,21 | 6 | 4 |
| AXLE | Steering Axle | Single(Drive)Axle | Tandem Axle Unit | Tridem Axle Unit |
| CONFIGURATION | Legal Mass=8t | Legal Mass=10t | Legal Mass=18t | Legal Mass=24t |
| | Legal ESA=2.16 | Legal ESA=1.45 | Legal ESA=3.93 | Legal ESA=3.68 |
| OVERLOAD (kg) | OVERLOAD FEE (ETB) | | | |
| 5200 | 30144 | 16428 | 15081 | 22891 |
| 5600 | 34563 | 18730 | 16755 | 24620 |
| 6000 | 39391 | 21229 | 18515 | 26420 |
| 6400 | 44651 | 23937 | 20365 | 28294 |
| 6800 | 50367 | 26863 | 22309 | 30243 |
| 7200 | 56567 | 30021 | 24350 | 32269 |
| 7600 | 63275 | 33421 | 26489 | 34375 |
| 8000 | 70520 | 37076 | 28732 | 36563 |

Scanned by CamScanner